ለማስናበት ተገዷል። እስካሁንም የተዘጉ ቢሮዎቹን ለመክፈት፣ የተሰናበቱ ሠራተኞቹን ለመተካት አልቻለም። ከምንም በላይ አሁን የቀሩትን 20 የማይሞሉ ሠራተኞቹን ለማቆየትም ሆነ ወር ጠብቆ ደመወዝ ለመክፍል ሲቸገር፣ የሰብዓዊ መብት ተቆርቋሪ ቅን ኢትዮጵያውያንን ብድር እና ስጦታ ሲለምን ቆይታል። ለበርካታ ወራት ለሠራተኞቹ ደመወዝ ለመክፈል ሲቸገር፣ ከታገደበት ገንዘብ በብድር እንኳን እንዲሰጠው ያቀረበው ጥያቄ ምላሽ ተነፍጎታል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በዘርፈ-ብዙ ችግሮች ከተተበተበችበት ለመውጣት ሁለንተናዊ የለውጥ እንቅስቃሴ በሚደረግበት በዚህ ወቅት ኢ/ሰመጉን የመሰሉ ሀገር-በቀል ሲቪል ማህበራት ያለባቸው የዜግነት ኃላፊነት እና ሊወጡት የሚችሉትን የማይተካ ሚና እንደነዚህ አይነት ችግሮች እየተገዳደሩት ይገኛል። ባለፉት 7 ወራት መንግስት የወሰዳቸው መልካም እርምጃዎች የዜጐች ሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩባት፣ የህግ ልዕልና የሰፈነባት ኢትዮጵያ ትኖረን ዘንድ መሠረታዊ መነሻ መሆናቸውና እና ለሀገር ግንባታ ሂደቱ ወሳኝ እንደሆኑ ሰመጉ በፅኑ ያምናል። ይህንን አቋሙንም በተደጋጋሚ በሰጣቸዉ ጋዜጣዊ መግለጫዎች አረጋግጧል። በዚህ አጭር ግዜ ውስጥ ለተሰሩት ስራዎች እውቅና መስጠት ብቻ ሳይሆን ሒደቱን በመደገፍ ረገድ በሙሉ አቅሙ ተቋማዊ ሃላፊነቱን እንደሚወጣም በዚህ አጋጣሚ በድጋሚ ያረጋግጣል።

**ክቡርነትዎ፤**

ባለፉት 9 አመታት በከፍተኛ የገንዘብ ሃይል እጥረት ሲንገታገት የቆየው የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ ሕልውና በጥያቄ ምልክት ውስጥ ይገኛል። ተቋሙ ላለፉት 27 ዓመታት ያበረከተውን ከፍተኛ አስተዋፅዖ ከግንዛቤ በማስገባት፣ ሕልውናውን በማቆየት በኢትዮጵያ ሕዝብ የተጣለበትን ከባድ ኃላፊነት መወጣቱን ይቀጥል ዘንድ የእርስዎን ድጋፍ ይፈልጋል። በዚህም ከሕግ አግባብ ውጪ የታገደበት ገንዘብ እንዲለቀቅ አስፈላጊውን ሁሉ እንዲያደርጉልን በታላቅ አክብሮት ጥያቄያችንን እናቀርባለን።

ከሠላምታ ጋር

አምሃ መኮንን

ሊቀመንበር - የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

Scanned by CamScanner